# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
# SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

# ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ
# DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፩ ወላይታ ሶዶ
ጥር ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 11 Wolaita Sodo
20, January 2024


## ደንብ ቁጥር ፲፩/፪ሺ፲፮

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ

በክልሉ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችንና የዶሮ ግብዓቶች ማቅረብ የአርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩን፣ የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ እና ለዚህም ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በክልሉ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችንና የዶሮ ግብዓቶችን ማቅረብ የሚያስችል ስራ የሚሰራ፣ ብቃት ያለው፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተወዳዳሪ የሆነ፣ እነዚህን ተግባራት በባለቤትነትና በተጠያቂነት የሚመራ ድርጅት በማቋቋምና አሰራር ስርዓት በመፍጠር ለአርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች ዶሮዎችንና ተያያዥ ግብዓቶችን ማቅረብ ወሳኝ በመሆኑ፤

## Regulation No. 11/2024

## South Ethiopia Regional State Chicken Breeding Enterprise Establishment Regulation

**WHEREAS,** providing improved breeds chickens and chicken inputs in the region has a vital role to ensure the benefit of the farmers, pastoralists, youths and women, and for which it is essential to create a favorable environment;

**WHEREAS,** it is important to provide chickens and related inputs to farmers/pastoralists, youths and women by establishing a competent, efficient, accessible and competitive enterprise that can provide improved breeds of chickens and chicken inputs in the region;

| | |
|---|---|
| ለክልሉ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች ወጣቶችና ሴቶች የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችና የዶሮ ግብዓቶች አቅርቦት ከፍላጎት ጋር እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ በሀገራዊ ፕሮግራሞች ከተቀመጡ ግቦች ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ፤ | **WHEREAS,** the supply of chickens and chicken inputs of improved breeds to the farmers, pastoralists, youths and women of the region needs to be aligned with the demand and the related goals set by the national programs; |
| በክልሉ በተለይ ለወጣቶችና ሴቶች በከተማና በገጠር የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችና የዶሮ ግብዓቶች በብዛት፣ በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋና በተገቢዉ ጊዜ ማቅረብ ያለዉ ፋይዳ ጉልህ በመሆኑና ይህም የክልሉን የስራ አጥነት ምጣኔ በመቀነስ ረገድ ትልቅ አቅም መሆኑ በመታመኑ፣ | **WHEREAS,** the benefit of providing improved breeds chickens and chicken iputs in quantity, quality, reasonable price and at the right time especially for the creation of jobs for the youths and women in urban and rural areas is significant and it is believed that this is a great potential in reducing the unemployment rate of the region; |
| የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችና የዶሮ ግብዓቶች ፍላጎት ጋር በተያያዘ ከክልላችን ባሻገር በሌሎች የሀገራችን ክልሎች ብሎም አጎራባች ሀገራት ያሉ የገበያ ዕድሎችን ጭምር በመለየት፣ አዋጭነት በማጥናት፣ በነፃ ገበያ ውስጥ ተወዳድሮ ውጤታማ በመሆንና ተገቢዉን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትና ትርፋማነት በማረጋገጥ በክልሉ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሂደት ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ሊወጣ የሚችል የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም ወሳኝ በመሆኑ፤ | **WHEREAS,** it is important to establish a chicken breedig enterprise that can play a significant role in the economic development of the region by identifying market opportunities in other regions of our country and neighboring countries beyond our region in relation to the demand for improved breeds of chickens and chicken inputs, studying the feasibility, competing in the free market and ensuring appropriate economic benefits and profitability; |
| የደቡብ አትዮጵያ ክልል መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት፤ የክልሉ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፭ አንቀፅ ፵፬፣ አንቀፅ ፵፭ ንዑስ አንቀፅ ፩ እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፶፩ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሠረት፤ ይህንን ደንብ አውጥቷል። | **NOW, THEREFORE,** the South Ethiopia Regional State Administrative Council, in accordance with the Proclamation issued to establish executive bodies, powers and functions of the regional government No. 3/2015 Article 44 and Article 45 Sub-Article 1, and the Public Enterprises Proclamation No. 17/2023 Article 51 Sub-Article 1, issued this |

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፲፩/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩ **"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፤

፪ **"መንግሥት"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ነው፤

፫ **"ተቆጣጣሪ ባለስልጣን"** ማለት የልማት ድርጅቶችን በተቀናጀ መንገድ ለመደገፍ፣ በተወዳዳሪነት መስራታቸውን ለማረጋገጥና ይልቁንም የክልሉ መንግስት በየትኛውም ድርጅት ላይ የሚኖሩትን የባለቤትነት መብቶች ለመጠበቅ ወይም ለማስከበር በክልሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፵፮ የተገለጸዉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ድጋፍና ክትትል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው፤

፬ **"ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የክልሉ መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ የተሻሻሉ የዶሮ ዝሪያዎችና ተያያዥ ግብዓቶች በማባዛት ወይም በማምረት ወይም በመግዛት የሚያቀርብ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ

regulation.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "South Ethiopia Regional State Chicken Breeding Enterprise Establishment Regulation No. 11/2024".

### 2. Definitions

In this regulation, unless the context dictates otherwise:

1) **"Region"** means South Ethiopia Region;

2) **"Government"** means the Regional Government of South Ethiopia;

3) **"Supervisory Authority"** means the support and monitoring authority of public enterprises established under article 46 of Public Enterprises Proclamation No. 17/2023 of the region to support public enterprises in a coordinated way, to ensure that they work competitively and rather to protect or enforce the ownership rights of the state government in any enterprise;

4) **"Enterprise"** means the South Ethiopia Chicken Breeding Enterprise, which is being a public enterprise of the state government, provides improved chicken breeds and related

| | |
|---|---|
| ነው፤ | inputs by reproduction or production or purchase; |
| ፭ **"ቦርድ"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ መሠረት የሚቋቋም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝን የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመራ የሥራ አመራር ነው፤ | 5) **"Board"** means the management board of the South Ethiopia Regional Government Chicken Breeding Enterprise established in accordance with Article 11 of this regulation; |
| ፮ **"የዶሮ ግብዓት"** ማለት በኢንተርፕራይዙ የሚቀርቡ ሆነው ለም ዕንቁላል፣ የአንድ ቀን ዕድሜ ያለው ጫጩት፣ ቄብና ኮክኔ፣ ክትባትና መድኃኒት፣ የተመጣጠነ የዶሮ መኖ፣ ኬሚካሎችንና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ግብዓቶችን ያጠቃልላል፤ | 6) **"Chicken inputs"** means fertile eggs, day-old chicks, pullet chicks and cockerel, vaccines and drugs, nutritional chicken feed, chemicals and other inputs as required; |
| ፯ **"የአንድ ቀን ዕድሜ ጫጩት"** ማለት በዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዙ ውስጥ የተፈለፈሉና የአንድ ቀን ዕድሜ ያላቸው ጫጩቶች ናቸው፤ | 7) **"A day-old chicks"** means one-day-old chicks hatched in the chicken breeding enterprise; |
| ፰ **"ቄብ ዶሮ"** ማለት በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የተፈለፈሉና የተዘጋጀላቸውን የተመጣጠነ መኖና አስፈላጊው ክትባት ያገኙ እንስት ዶሮዎች ናቸው፤ | 8) **"Pullet chickens"** means female chickens that have been hatched in the enterprise and that have received the necessary nutritious feeds and vaccinations prepared for them; |
| ፱ **"ኮክኔ ዶሮ"** ማለት በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የተፈለፈሉና የተዘጋጀላቸውን የተመጣጠነ መኖና አስፈላጊውን ክትባት ያገኙ ተባዕት ዶሮዎች ናቸው፤ | 9) **"Cockerel chicken"** means male chickens that have been hatched and that have received the necessary nutritious feeds and vaccinations prepared for them; |
| ፲ **"ለም ዕንቁላል"** ማለት በኢንተርፕራይዙ ከተመረቱ እንቁላሎች ውስጥ ለዘርነት የተመረጠ ዕንቁላል ነው፤ | 10) **"Fertile egg"** means an egg selected for breeding from the eggs produced by the enterprise; |
| ፲፩ **"የዶሮ መኖ"** ማለት በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ለሚገኙ ዶሮዎች አስፈላጊውን ንጥረ ነገር የያዘ የተመጣጠነ የዶሮ ምግብ ነው። | 11) **"Chicken feed"** means a nutritious chicken feed containing the necessary nutrients for chickens of different ages; |
| ፲፪ **"የዶሮ በሽታ"** ማለት በዶሮዎች ላይ የሚደርስ | 12) **"Chicken disease"** means a disease affecting |

| | |
|---|---|
| የጤና መታወክ ነው፤ | chickens; |
| ፲፫ **“የምርት ወጪ”** ማለት ምርት ለማምረት የሚወጣ ወጪ እንደ ጥሬ ዕቃ፣ ጉልበት፣ የምርት ፍጆታ አቅርቦቶች፣ የአገልግሎት ክፍያዎች (የኤሌክትሪክ፣ ውሃ፣ ወዘተ)፣ ቋሚ የማምረቻ መሳሪያዎች የእርጅና ተቀናሽ፣ የመንግስት ግብር እና ሌሎች ከምርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች ያጠቃልላል፤ | 13) **“Production cost”** means the cost of producing a product such as raw materials, labor, consumables, service charges (electricity, water, etc.), depreciation of fixed production equipments, government taxes and other costs related to production; |
| ፲፬ **“ጠቅላላ ወጪ”** ማለት የምርት ወጪ እና የምርት ወጪ ያልሆኑ በሂሣብ ዓመቱ ውስጥ ለስራ ማስኬጃ፣ ለደመወዝ፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ወለድና ልዩ ልዩ ታክሶች ወጭ የተደረጉ ሂሣቦች የሚያካትት ነው፤ | 14) **“Total Cost”** means the cost of production and non-production costs, including the costs incurred during the accounting year for operating expenses, wages, depereciation expenses, interest expenses and miscellaneous taxes; |
| ፲፭ **“ገቢ”** ማለት በኢንተርፕራይዙ ከምርትና ተረፈ ምርት ሽያጭ፣ ከአገልግሎት ሽያጭ እና ኢንተርፕራይዙ በራሱ ከመነጨ ሌሎች የገቢ ማስገኛ ምንጮች የሚሰበሰብ ገቢ ነው፤ | 15) **“Revenue”** means the income collected by the enterprise from the sale of products and by-products, from the sale of services and from other sources of income generated by the enterprise itself; |
| ፲፮ **“የተጣራ ትርፍ”** ማለት ከገቢዎችና ከሌሎች ክፍያዎች ከተገኘው ገንዘብ ላይ የምርት ወጭዎችና በሂሣብ ዓመቱ ውስጥ ለስራ ማስኬጃም ሆነ ለደመወዝ ባግባቡ ወጭ የተደረጉ ሂሣቦች፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ወለድና ልዩ ልዩ ታክሶች ተቀንሰው የሚቀረው ሂሣብ ነው፤ | 16) **“Net profit”** means the sum of money received from income and other payments after deducting expenses and reasonable expenses incurred during the financial year for operating and salaries, retirement allowance, interest and miscellaneous taxes; |
| ፲፯ **“ጠቅላላ ንብረት”** ማለት የኢንተርፕራይዙ ተንቀሣቃሽና ኢ-ተንቀሣቃሽ ሀብት ሲሆን የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ፣ ተቀማጭ የባንክ ሂሣቦች፣ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣ ግዙፍነት የሌላቸዉ ንብረቶች፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎችና ወጪዎች ያልሆኑ ሌሎች ሂሣቦችን | 17) **“Total Assets”** means the enterprise's movable and immovable assets and includes the enterprise's cash, bank deposits, accounts receivable, intangible assets, prepaid expenses |

| | |
|---|---|
| ያጠቃልላል፤ | and other accounts that are not expenses; |
| ፲፰ **“የተጣራ ጠቅላላ ንብረት”** ማለት ከጠቅላላ ንብረት ላይ በተያዘው የሂሳብ ዓመት ውስጥ የሚከፈሉ ዕዳዎች፣ በረጅም ጊዜ የሚከፈሉ ዕዳዎች፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገቢና ሌሎች ዕዳዎች ተቀንሰው የሚቀረው ንብረት ነው፣ | 18) **“Net total assets”** means total assets less liabilities payable in the accounting year, long-term liabilities, prepaid income and other liabilities; |
| ፲፱ **“መነሻ ካፒታል”** ማለት ኢንተርፕራይዙ በተቋቋመበት ጊዜ በክልሉ መንግስት አማካኝነት የተመደበለት የተጣራ ጠቅላላ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፤ | 19) **“Initial capital”** means the value of the net total assets allocated to the enterprise at the time of its establishment by the state government; |
| ፳ **“ካፒታል”** ማለት ኢንተርፕራይዙ በተቋቋመበት ጊዜና ከዚያ በኋላ በክልሉ መንግስት አማካኝነት የሚመደብለት የተጣራ ጠቅላላ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፤ | 20) **“Capital”** means the value of the enterprise at the time of its establishment and at the time of allocation of the net total assets allocated to it by the state government; |
| ፳፩ **“ኦዲተር”** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ /፳፬/ ስር በተመለከተው መሠረት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝን ሂሣብ እንዲመረምር የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤ | 21) **“Auditor”** means a natural person or a body authorized by law to audit the accounts of South Ethiopia Poultry Breeding Enterprise according to Article 24 of this regulation. |
| ፳፪ **“የመንግስት የትርፍ ድርሻ”** ማለት ከተጣራው ትርፍ ላይ ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሣቦች ገቢ የሚደረገው ገንዘብ ተቀንሶ የቀረው ሂሣብ ነው፤ | 22) **“Government's profit share”** means the net profit after deducting the money transferred to the legal reserve account and other reserve accounts; |
| ፳፫ **“ማዕከል”** ማለት በኢንተርፕራይዙ ሥር የተቋቋሙ ወይም የሚቋቋሙ አምራች ማዕከላት ናቸው፤ | 23) **“Center”** means production centers established or to be established under the enterprise; |
| ፳፬ **“የጫጩት ማሳደጊያ”** ማለት ከኢንተርፕራይዙ | 24) **“Chick rearing shed”** means centers where |

ቀጥታ በመረከብ የአንድ ቀን ጫጩቶች የሚያድጉበት ማዕከላት ማለት ነው፤

፳፭ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

**፫ <u>የፆታ አገላለጽ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተቀመጠው አገላለጽ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

**፬ <u>የደንቡ የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ በሚቋቋሚባቸው ቦታዎች፣ የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝን በሚመለከቱ ጉዳዮች፣ በኢንተርፕራይዙ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞችና የቦርድ አባላት ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለ ኢንተርፕራይዙ መቋቋም፣ ተጠሪነት እና ዓላማ</u>

**፭ <u>መቋቋምና ተጠሪነት</u>**

፩ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዙ" እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለዉ የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪ የኢንተርፕራይዙ ተጠሪነት ለሥራ አመራር ቦርዱ ይሆናል።

**፮ <u>ዓላማ</u>**

day-old chicks are reared directly from the enterprise;

25) **"Person"** means a natural or juidicial person.

**3. <u>Gender Reference</u>**

Any expression in the masculine gender in this regulation includes the feminine gender.

**4. <u>Scope of Application</u>**

This regulation shall be applicable to the areas where the South Ethiopia chicken breeding enterprise is established, to all matters related to the chicken breeding enterprise, to the officers, employees and board members of the enterprise.

## <u>PART TWO</u>
## <u>ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY AND PURPOSE OF THE ENTERPRISE</u>

**5. <u>Establishment and Accountability</u>**

1) South Ethiopia Regional State Chicken Breeding Enterprise, hereinafter referred to as "the Enterprise" has been established as a public enterprise of the regional government with legal personality.

2) The enterprise shall be accountable to the management board.

**6. <u>Purpose</u>**

| | |
|---|---|
| ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡- | The purposes for which the enterprise was established are as follows: |
| ፩ በክልሉ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችንና የዶሮ ግብዓቶች ማቅረብ የሚያስችል ስራ የሚሰራ፣ ብቃት ያለው፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ዘርፉን በባለቤትነትና በተጠያቂነት የሚመራ አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት በመፍጠር የክልሉን አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ውጤታማ የሆኑና የተሻሻሉ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችንና ተያያዥ ግብዓቶችን ማቅረብ፤ | 1) To provide improved breeds of chickens and chicken inputs to farmers, pastoralists, youths and women in the region by establishing a competent, efficient, accessible and competitive enterprise and systems of operation; |
| ፪ ለክልሉ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችና የዶሮ ግብዓቶች አቅርቦት ከፍላጎት ጋር እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ ሀገራዊ ፕሮግራሞች ከተቀመጡ ግቦች ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፤ | 2) To ensure that the supply of improved breeds of chickens and chicken inputs to the farmers, pastoralists, youths and women of the region is consistent with the needs and the goals set by related national programs; |
| ፫ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችና የዶሮ ግብዓቶች በብዛት፣ በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋና በተገቢዉ ጊዜ በማቅረብ በከተማና በገጠር ለወጣቶችና ሴቶች የስራ ዕድል በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸዉን ማሳደግ፤ | 3) To increase the economic benefits for the youths and women in urban and rural areas by creating job opportunities through providing improved breeds of chickens and chicken inputs in quantity, quality, reasonable price and at the right time; |
| ፬ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች እና የዶሮ ግብአቶች አቅርቦት በተመለከተ ከክልላችን ባለፈ በሌሎች የሀገራችን ክልሎችና አጎራባች ሀገራት ያሉ የገበያ እድሎች በመለየት፣ አዋጭነት በማጥናት፣ በገበያ ላይ ውጤታማ በሆነ መንገድ በመወዳደር፣ ተገቢውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅምና | 4) To ensure appropriate economic benefits and profitability by identifying market opportunities in other regions of our country and neighboring countries beyond our region, studying feasibility, and competing effectively in the market in relation to the supply of improved breeds of chickens and chicken inputs; |

ትርፋማነት ማረጋገጥ፤

፭ ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መስራት፤

## ፯ የዋና መሥሪያ ቤትና ቅርንጫፎች አድራሻ

የኢንተርፕራይዙ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ ዲላ ከተማ ሆኖ አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች በስሩ ተጠሪ የሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም ማዕከላት ይኖሩታል።

# ክፍል ሦስት
# ስለ ኢንተርፕራይዙ አወቃቀር፣ ሥልጣንና ተግባር

## ፰ የኢንተርፕራይዙ አደረጃጀት

፩ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፤

፪ የሥራ አመራር ቦርድ፤

፫ ዋና ስራ አስኪያጅ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጆች፤

፬ ዓላማውን ለመፈፀምና ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የበታች ስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እና መዋቅሮች፤ ይኖሩታል።

## ፱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣ ስልጣንና ተግባር

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ባወጣዉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፵፮ የተደነገገዉ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሆኖ በአንቀጽ ፵፯ የተጠቀሱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

## ፲ የኢንተርፕራይዙ ስልጣንና ተግባር

5) To do other related tasks that help to help achieve the goal.

## 7. Address of the Head Office and Branches

The address of the head office of the enterprise shall be at Dilla town and may have branch offices or centers elsewhere in other places as necessary.

# PART THREE
# ORGANIZATION, POWERS AND DUTIES OF THE ENTERPRISE

## 8. Organization of the Enterprise

1) Supervisory Authority;
2) Management Board;
3) A General Manager and Deputy Managers as necessary;
4) Other subordinates, staffs and structures needed to carry out and realize its purposes.

## 9. Supervisory Authority, Powers and Duties

The supervisory authority shall be the one stipulated in Article 46 of Public Enterprises Proclamation No. 17/2016 issued by the South Ethiopia Regional Government, and shall have the powers and duties stipulated in Article 47 of the Proclamation.

## 10. Powers and Duties of the Enterprise

The enterprise shall have the following powers and duties under this regulation:

1) Builds, manages and leases out chick hatching

ኢንተርፕራይዙ በዚህ ደንብ መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩ በክልሉ የተሻሻለ ዶሮ ዝርያዎችን ለማባዛትና ለማሳደግ የሚያገለግሉ የጫጩት ማስፈልፈያና የጫጩት ማሳደጊያ ማዕከላትን እንዲገነቡ ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በሊዝ ያከራያል፤

፪ ለክልሉ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች፣ የገጠርና የከተማ ህብረተሰብ ተፈላጊ የሆኑ የተሻሻሉ ዶሮዎችን በማባዛት ለም ዕንቁላል፣ የአንድ ቀን ዕድሜ ያለው ጫጩት፣ ቄብና ኮክኔ በሚፈለገው መጠንና በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል፤

፫ በኢንተርፕራይዙ ለሚሰራጩ የአንድ ቀን ዕድሜ ያለው ጫጩት አስፈላጊ የሆኑ የተመጣጠነ መኖ፣ ክትባት እና መድሐኒት ያቀርባል፤

፬ በዶሮ ብዜት ለሚሰማሩ በቡድንና በማህበር ለተደራጁ ወጣቶችና ሴቶች፣ ሞዴል አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ግለሰቦች የስልጠናና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፭ የኢንተርፕራይዙን ዓላማ ለማሳካት ከታመነበት በሥራው ልምድና ፍላጎቱ ካላቸው የሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ከሚገኙ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር የቴክኒክ ትብብር ወይም የሥራ አመራር ወይም በአክሲዮን መልክ በህጋዊ ውል ይሠራል፤ ከዚህ አኳያ፦

ሀ/ በዶሮ ኢንተርፕራይዝ ሥር ካሉት እርባታ ማዕከላት በየጊዜው አፈፃፀሙ እየታየ በሚታደስ ሊዝ እንዲተዳደር ሊሰጥ ይችላል፤

and chick rearing centers used for breeding and raising improved chicken breeds in the region;

2) Supplies fertile eggs, one-day-old chicks, pullet chickens and cockerel chickens in the required quantity and at reasonable prices by breeding/rearing of improved chickens that are needed by farmers/pastoralists, youths and women, rural and urban society of the region;

3) Provides necessary nutritional feed, vaccination and drugs to a day-old chicks distributed by the enterprise;

4) Provides training and counseling services to young people and women, model farmers/pastoralists and individuals organized in groups and associations engaged in chicken breeding;

5) If it is trusted to achieve the purpose of the enterprise, will work with local and foreign organizations and individuals who have the experience and interest in the work through technical cooperation or management or legal contracts in the form of shares; accordingly,

a) Breeding centers under the Chicken Enterprise may be managed on a renewable lease basis with periodic performance reviews;

b) Chicken centers are managed by the chicken breeding enterprise and may be

ለ/ የዶሮ እርባታ ማዕከላት የሚተዳደሩት በዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ ሆነው በኪራይ ወይም በሊዝ ሊሰጡ ይችላሉ፤

፮ እንድአስፈላጊነቱ ከክልላችን ዉጭ ያሉ የገበያ ዕድሎችን በመለየት፣ አዋጭነት በማጥናት እና በገበያ ውስጥ ተወዳድሮ ውጤታማ ለመሆን ይሰራል፤

፯ በህግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፰ በሚያገኘው ገቢ ራሱን ያስተዳድራል፣ አቅሙንም ያጎለብታል፤

፱ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሰረት ውሎችን ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲ የዶሮ ዕርባታ ማዕከላትን ያስተዳድራል፣ ያቋቁማል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

፲፩ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ያከናዉናል፡፡

## ፲፩ ስለ ቦርድ መቋቋም

፩ በኢንተርፕራይዙ ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ የሥራ አመራር አካል በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪ የስራ አመራር ቦርድ አመሰራረት፣ የአባላት ተዋጽኦና የአገልግሎት ዘመን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ባወጣዉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፲፪ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፤

rented or leased;

6) As necessary, works by identifying market opportunities outside our region, studying feasibility and competing in the market effectively;
7) Hires, manages and dismisses workers in accordance with the law;
8) Adminnisters and capacitates itself with the income it earns;
9) Owns properties, enters into contracts according to the law, sues and be sued in his name;
10) Establishes and manages chicken breeding centers, the detail shall be determined by directive;
11) Performs other related duties that help to achieve its purpose.

## 11. Establishment of the Management Board

1) In the enterprise, a management body hereinafter called the "Board", is established by this regulation;

2) The formation of the management board, the composition of the members, and the term of service shall be in accordance with the provisions of Article 12 of the Public Enterprises Proclamation No. 17/2023 that has been issued by the South Ethiopia regional government;

| | |
|---|---|
| ፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተገለጸዉ ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፦ | 3) Subject to the general provision stated in sub article 1 of this article: |
| ሀ/ የቦርዱ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፤ | a) The board shall be accountable to the head of the state; |
| ለ/ የቦርዱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ ቢያንስ ሰባት አባላት ያሉት ሆኖ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሰየማሉ፤ | b) The members of the board, including the chairperson, shall be at least seven members and be appointed by the head of the state; |
| ሐ/ የቦርዱ አባላት በኢንተርፕራይዙ ስራ ላይ ለሚያሳልፉት ጊዜ አበል ሊከፈላቸው ይችላል፤ ዝርዝሩ አግባብ ባለዉ ህግ ይወሰናል። | c) Board members may be paid an allowance for the time spent on the business of the enterprise; the details shall be determined by applicable law. |
| **፲፪ <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>** | **12. <u>Powers and Duties of the Board</u>** |
| ፩ የኢንተርፕራይዙ ሥራ አመራር ቦርድ በክልሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፰ አንቀጽ ፲፫ ለሥራ አመራር ቦርድ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤ | 1) The management board of the enterprise shall have the powers and duties given to the management board in Article 13 of the state Public Enterprises Proclamation No. 17/2016; |
| ፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አመራር ቦርዱ ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦ | 2) Subject to the general provisions of sub-article 1 of this article, the management board shall have the following powers and duties: |
| ፩ የኢንተርፕራይዙን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤ | i) Leads, coordinates and supervises the work activities of the enterprise; |
| ፪ ኢንተርፕራይዙ የሚመራባቸውን የተለያዩ መመሪያዎች ያፀድቃል፣ በተግባር ላይ መዋላቸውንም ያረጋግጣል፤ | ii) Approves the various directives that govern the enterprise and ensures that they are implemented; |
| ፫ የኢንተርፕራይዙን ዕቅድ፣ በጀትና | iii) Examines and approves the enterprise's |

| | |
|---|---|
| የድርጊት መርሃ-ግብር መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይመራል፤ | plan, budget and action plans, follows up their implementation, leades; |
| ፬ በኢንተርፕራይዙ ተቋማዊ አወቃቀርና የሰው ሃይል ግንባታ ረገድ በሚቀርቡለት ጥያቄዎች ላይ ውሣኔዎችን ይሰጣል፤ | iv) Gives decisions on the questions presented to it regarding the institutional structure and building of human resources of the enterprise; |
| ፭ የሥራ አስኪያጁንና የሠራተኞችን ደረጃ፣ ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅምና ማበረታቻ የተቋሙንና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ ያስጠናል፣ በርዕሰ መስተዳድሩ ያስወስናል፣ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤ | v) Makes the level, salary, benefits and bonuses of the manager and employees be studied by taking in to account the institution’s and the regions objective condition; makes the same to be approved by head of the state as well as follows-up and ensures its implementation; |
| ፮ የኢንተርፕራይዙ ሀብትና ንብረት በአግባቡ መያዙንና መጠበቁን፣ የገንዘብና የሰው ኃይል አጠቃቀሙም የተቋሙን ዓላማዎች ለማስፈፀም የዋለ ስለመሆኑ በቅርብ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤ | vi) Closely monitors and ensures that whether the resources and assets of the enterprise are properly managed and protected, and that the financial and human resources usage has been to implement and fulfill the objectives of the institution; |
| ፯ የኢንተርፕራይዙ የገንዘብና ንብረት ኦዲት በየዓመቱ እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እንዲከናወን በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ኦዲተር እንዲመደብ መደረጉን፣ ኦዲት መከናወኑን፣ የኦዲት ሪፖርቱ መጽደቁን፣ ወዘተ በቅርበት ይከታተላል፣ የኦዲት ውጤቱ ላይ ይወያያል፣ ለኢንተርፕራይዙ አመራር ተገቢዉን ግብረመልስና የስራ | vii) Closely monitors the appointment of an auditor by the supervisory authority to conduct the financial and property audit of the enterprise every year and when necessary, whether the audit has been carried out, the approval of the audit report, etc., discusses the audit results, |

| | |
|---|---|
| መመሪያ ይሰጣል፤ | and gives appropriate feedback and work instructions to the management of the enterprise; |
| ፰ በፋይናንስ ህግ ላይ ተመርኩዞ ሊመለስ የማይችል ተብሎ የታመነበትን ወይም የተረጋገጠ ንብረትና ገንዘብ ከድርጅቱ መዝገብና ሂሳብ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ | viii) Based on the financial law, submits to the relevant body to write-off the property and money that is believed or proven to be irretrievable from the records and accounts of the enterprise, and monitors the performance; |
| ፱ በኢንተርፕራይዙ ስራ አስኪያጅ አማካይነት በሚቀርቡለት ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤ | ix) Decides on other relevant issues submitted to it through the enterprise's manager; |
| ፲ የኢንተርፕራይዙን ዓላማ ለማሳካት በሥራው ልምድና ፍላጎት ካላቸው የሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ከሚገኙ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር የቴክኒክ ትብብር ወይም የሥራ አመራር ወይም በአክሲዮን መልክ እንዲሰራ ይወስናል፤ ከዚህ አኳያ፦ | x) In order to achieve the purpose of the enterprise, decides to work with local and foreign organizations and individuals who have experience and interest in the work, technical cooperation or management or in the form of shares; accordingly, |
| ሀ/ በዶሮ ኢንተርፕራይዝ ሥር ካሉት የእርባታ ማዕከላት በየጊዜው አፈፃፀሙ በሥራ አመራር ቦርድ እየተገመገመ በሚታደስ ሊዝ እንዲተዳደሩ ወይም የተሻለ አሰራር ካለም አጥንቶ ሊወስን ይችላል፤ | a) The board up on periodically evaluating the performance of the centers under the Chicken Breeding Enterprise, may study and decide whether the centers shall be managed by a renewable lease or if there is a better practice; |
| ለ/ የዶሮ እርባታ ማዕከላት የሚተዳደሩት በዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ ሆነው እንደአስፈላጊነቱ አዋጭነታቸው እየታየ በሥራ አመራር ቦርድ እየተወሰነ በውል ለወጣቶች ወይም ለግለሰብ ወይም ሌላ በመስኩ | b) Chicken breeding centers are managed by the Chicken Breeding Enterprise, the management board based on their feasibility may decide |

ለሚሰማራ አካል በኪራይ ወይም በሊዝ ሊሰጡ ይችላሉ፤

፲፩ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎችንና ተዛማጅ ግብዓቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ፣ ወጣቶችና ሴቶች እንዲቀርብ የማምረቻና መሸጫ ዋጋ ተጠንቶ በሚቀርብለት መሠረት መርምሮ ይወስናል፤

፲፪ እንደአስፈላጊነቱ በኢንተርፕራይዙ ሥር አዳዲስ የዶሮ እርባታ ማዕከላት እንዲቋቋሙ ይወስናል፤

## ፲፫ <u>ስለቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት</u>

፩ ቦርዱ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎች ሊኖሩት ይችላል፤

፪ የቦርድ አባላት ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት የመወያያ አጀንዳው በጽሑፍ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ያስፈልጋል፤

፫ ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ-ጉባኤ ይሆናል፤

፬ ማናቸውም ጉዳይ ለቦርዱ ቀርቦ ከተመከረበት በኋላ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምፅ የተደገፈ እንደሆነ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለኩል የተከፈለ እንደሆነ የሰብሳቢውን ድጋፍ ያገኘው ሀሣብ የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል፤

፭ ቦርዱ ከድርጅቱ ሰራተኞች መካከል ፀሀፊውን

that the centers be rented or leased to youths or individuals or other entities engaged in the field under a contract;

xi) Investigates and determines the production and selling price of improved breeds of chickens and related resources at affordable prices to farmers, youths and women;

xii) Determines the establishment of new chicken breeding centers under the enterprise as necessary;

## 13. <u>Timing of Board Meeting and Decision-Making Procedure</u>

1) The Board shall hold its regular meeting at least once in three months, and may have emergency meetings as necessary;

2) It is required that the board members receive the agenda in writing before the meeting;

3) If more than half of the board members attend the meeting, it will be a quorum;

4) After any issue has been presented to the board and discussed up on, it will be passed on as a decision of the board if supported by the majority of the members present at the meeting. However, if the vote is equally divided, the decision of the board shall be the opinion supported by the chairman;

መርጦ ሊመድብ ይችላል፤

፮ ፀሀፊው ቦርዱ የሚያካሂደውን የእያንዳንዱን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ በሚገባ ይይዛል፣ በስብሰባው ላይ የተገኙት አባላትም በቃለ-ጉባኤው ላይ ይፈርሙበታል፤

፯ የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ በአካል ሊገኝና ሊሳተፍ ይችላል፤ ሆኖም ቦርዱ በሚያሳልፋቸው ማናቸውም ውሣኔዎች ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፤

፰ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል

## ፲፬ ስለ ቦርድ አባላት ተጠያቂነት

፩ የቦርድ አባላት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጧቸውን ተግባራት በከፍተኛ ትጋትና በብርቱ ጥንቃቄ መፈፀም አለባቸው፤

፪ አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ካለመፈፀማቸው የተነሣ በኢንተርፕራይዙ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

## ፲፭ የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪነትና ስልጣን

፩ የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፤

፪ የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ በክልሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር

5) The board may choose and appoint the secretary from among the company's employees;

6) The secretary shall keep the minutes of each meeting held by the board, and the members present at the meeting shall sign the minutes;

7) The general manager of the enterprise may attend and participate in the board meetings; however, shall not have the right to vote on any of the resolutions the board passes on;

8) Subject to the provisions of this article, the board may issue its own detailed meeting time and decision-making procedure guidelines.

## 14. Accountability of Board Members

1) Board members must perform their duties under this regulation with great diligence and diligence;

2) The members will be jointly and severally responsible for the damage caused to the organization due to their failure to perform their duties properly.

## 15. Powers and Duties of the General Manager of the Enterprise

1) The general manager of the enterprise shall be accountable to the board;

2) The general manager of the enterprise shall

| | |
|---|---|
| ፲፯/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፲፮ የተደነገጉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤ | have the detailed powers and duties stipulated in Article 6 of the Public Enterprises Proclamation No. 17/2016 of the state; |
| ፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋና ስራ አስኪያጁ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ ድንጋጌዎች ስር ለኢንተርፕራይዙ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤ | 3) Subject to the general provision referred to in sub-article 2 of this article, the general manager shall have the powers and duties assigned to the enterprise under the provisions stated in Article 10 of this regulation; |
| ፬ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ስራ አስኪያጁ ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤ | 4) Subject to the general provisions of sub-articles 2 and 3 of this Article, the general manager shall have the following powers and duties: |
| ሀ/ የኢንተርፕራይዙን የዕለት ተዕለት ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤ | a. Leads, manages and supervises the daily operations of the enterprise; |
| ለ/ የኢንተርፕራይዙን ዕቅድ፣ በጀትና የድርጊት መርሃ-ግብር ይነድፋል፣ በቦርዱ ሲፀድቅ ይፈጽማል፣ ወቅታዊ የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፤ | b. Designs the enterprise's plan, budget and action plan, executes it when approved by the board, and submits current performance and financial reports to the board; |
| ሐ/ በድርጅቱ የውስጥ ደንብና አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሌሎች የድርጅቱን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያዛዉራል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዝና አበሎቻቸውን ይወስናል፤ | c. Hires, assigns, transfers, dismisses, and determines the salaries and allowances of other employees in accordance with the public enterprise's internal regulations and other relevant laws; |
| መ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንተርፕራይዙን ይወክላል፤ | d. Represents the enterprise in dealings with third parties; |
| ሠ/ በኢንተርፕራይዙ ስም የባንክ አካውንት ይከፍታል፣ ከሌሎች ከሚወከሉ የሥራ ኃላፊዎች ስምና በጣምራ ፊርማ በጋራ | e. Opens a bank account in the name of the enterprise, and operates the account |

ሂሳቡን ያንቀሳቅሳል፤

ረ/ በኢንተርፕራይዙ የሥራ ዕቅድና በጀት መሠረት አስፈላጊ ክፍያዎችን በሕግ መሠረት እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤

ሰ/ እንደአስፈላጊነቱ ከስልጣኑ በከፊል ለኢንተርፕራይዙ የበታች የስራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ሸ/ ሌሎች በቦርዱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

**፲፮ <u>የምክትል ስራ አስኪያጅ ኃላፊነትና ተግባር</u>**

፩ ተጠሪነቱ ለዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ በኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

፪ ዋና ስራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፲፯ <u>ስለ ኢንተርፕራይዙ መፍረስ፣ መዋሃድ ወይም መከፋፈል</u>**

የክልሉ መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፮ በተጠቀሱ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ኢንተርፕራይዙ እንዲፈርስ፣ ከሌላ የልማት ድርጅት ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈል ወይም እንዲሸጥ

jointly with the names and signatures of other representatives;

f. According to the business plan and budget of the enterprise, makes necessary payments according to the law;

g. Delegate part of his authority to subordinate officials of the enterprise as necessary;

h. Performs other duties assigned by the board;

**16. <u>Powers and Duties of the Deputy Manager</u>**

1) He is accountable to the general manager and performs the tasks assigned by the general manager of the enterprise;
2) When the General Manager is absent or unable to carry out his duties, shall act in his stead.

## <u>PART FOUR</u>
## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**17. <u>Dissolution, Merger or Split-Off of the Enterprise</u>**

When necessary, the regional government may decide that the enterprise shall be dissolved, merged with another public enterprise or split-off or

ሊወሰን ይችላል።

**፲፰ ካፒታል**

የኢንተርፕራይዙ የተከፈለ ካፒታል ብር ሁለት ቢሊዮን /፪ ቢሊዮን ብር/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር አምስት መቶ ሚሊዮን /፭፻ ሚሊዮን ብር/ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት በቅድሚያ ይከፈላል።

**፲፱ በዕዳ ስላለመጠየቅ**

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ሊጠየቅ አይችልም።

**፳ የኢንተርፕራይዙ የፋይናንስ ምንጭ**

ኢንተርፕራይዙ የሚከተሉት ዋና ዋና የፋይናንስ ምንጮች ይኖሩታል፡-

፩ በክልሉ መንግስት የሚመደብ ማቋቋሚያና ድጋፍ፤

፪ ከምርትና ከተረፈ ምርት ሽያጭ የሚሰበሰብ ገቢ፤

፫ ከኪራይና ሊዝ ጨምሮ ከሚሰጣቸው የተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎች፤

፬ ከተለያዩ አካላት የሚገኝ ድጋፍ፤

፭ ከባንክ የሚገኝ ብድር፤ ይሆናል።

**፳፩ የሒሳብ አያያዝ ስርዓት፣ የሂሳብ ዓመት፣ ሒሳብ መዝጋትና ዓመታዊ ሪፖርት**

፩ ኢንተርፕራይዙ በንግድ አሰራር ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ይኖረዋል፤

፪ የኢንተርፕራይዙ የበጀት ዓመት የመንግስት

sold in accordance with the relevant provisions of Pulic Enterprises Proclamation No. 17/2013.

## 18. Capital

The paid-up capital of the enterprise shall be two billion birr /2,000,000,000/, of which five hundred million birr /500,000,000/ shall be paid in advance in cash and in kind.

## 19. Liability

The enterprise cannot be held in debt in excess of its total assets.

## 20. Source of Finance for the Enterprise

The enterprise shall have the following major sources of finance:

1) Finance allocated by the state government for establishment and support;
2) Revenue from the sale of products and by-products;
3) From various service charges including rent and lease;
4) Support from various entities;
5) Bank Loans.

## 21. Accounting System, Accounting Year, Closing of Accounts and Annual Report

1) The enterprise shall maintain records by following generally accepted accounting principles.

| | |
|---|---|
| የበጀት ዓመት ይሆናል፤ | 2) The accounting period of the enterprise shall be the fiscal year of the government; |
| ፫ ኢንተርፕራይዙ በዓመት አንድ ጊዜ ሂሳቡን ይዘጋል፤ ዓመታዊው ሂሳብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የሚዘጋ ይሆናል። | 3) The enterprise closes its accounts once a year; the annual accounts shall be closed within three months following the end of the financial year. |
| **፳፪ <u>ስለመጠባበቂያ ሂሣቦችና አጠቃቀም</u>** | **22. <u>Reserve Accounts and Utilization</u>** |
| ፩ ኢንተርፕራይዙ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ይይዛል፤ | 1) The enterprise shall maintain a legal reserve account; |
| ፪ በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንተርፕራይዙ ከተጣራ ትርፉ ላይ ፭ በመቶ በየዓመቱ እያነሳ ፳ ከመቶ እስኪያህል ድረስ ወደ መጠባበቂያ ሂሣቡ ያስገባል፤ | 2) Without prejudice to the provisions provided in other laws otherwise, the enterprise shall annually transfer 5% of its net profit to the legal reserve account until such reserve account reaches 20% of the enterprise's capital; |
| ፫ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣቡ ኪሣራን ለመሸፈን፣ ያልታሰቡ ወጪዎችንና ዕዳዎችን ለመሸፈን ሊውል ይችላል፤ | 3) The legal reserve account shall be used to cover losses incurred by the enterprise, unforeseen expenses, and liabilities; |
| ፬ ከላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱን እያስፈቀደ ሌሎች መጠባበቂያ ሂሣቦች እንዲያዙ ለማድረግና አጠቃቀማቸውንም ለመወሰን ይችላል። | 4) Notwithstanding the above provision of this Article, may decide to maintain other reserve accounts and deterrmine their utilization up on permission of the Board. |
| **፳፫ <u>የመንግሥት የትርፍ ድርሻ ክፍያ</u>** | **23. <u>Payment of State Government Dividend</u>** |
| ኢንተርፕራይዙ ሂሣብ ዓመቱ ከተፈጸመበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሰባት ወራት ውስጥ የክልሉን መንግሥት የትርፍ ድርሻ ለመንግሥት ፈሰስ ያደርጋል። | The enterprise shall remit the profit share of the state government to the government within seven months from the end of the accounting year. |

## ፳፬ <u>የኦዲተሮች አመዳደብ</u>

፩ በሌላ ሕግ ለዋናው ኦዲተር የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢንተርፕራይዙ ሂሣብ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች ይመረመራል፡ ፡

፪ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በዋናው ኦዲተር የወጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉና ከማናቸውም ዓይነት ተጽእኖ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤

፫ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የውጭ ኦዲተሮችን የሥራ ጊዜ ይወሰናል፡፡

## ፳፭ <u>ሂሣብ የማስመርመር ግዴታ</u>

፩ የኢንተርፕራይዙ ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጪ `ያደረገ፣ የከፈለ ወይም ለሂሳቡ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሣቡን የማስመርመርና አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

፪ ማኘኛውም ሰው ሂሳቡን እንዲያስመረምር በኦዲተር ሲጠየቅ ፈቃደኛ ካልሆነ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፫ የኢንተርፕራይዙን ሂሳብ በወቅቱ አለመዝጋት በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡

## 24. <u>Appointment of Auditors</u>

1) Subject to the powers and functions given to the Office of the Chief Auditor of the State by other laws, the accounts of the enterprise shall be examined by the external auditors appointed by the supervisory authority;

2) The supervisory authority shall ensure that the external auditors it appoints meet the standards issued by the regional auditor's office and are free from any influence;

3) The supervisory authority shall determine the duration of service of the external auditors.

## 25. <u>Obligation for the Audit of Accounts</u>

1) Any person who receives, spends, pays or is responsible for the enterprise's money or property is obliged to examine the account and provide the necessary information when asked;
2) Any person who refuses to provide the accounts for audit when asked by the auditor shall be liable under the relevant law;
3) Failure to close the accounts of the enterprise on time shall bring a liability.

## 26. <u>Duty to Cooperate</u>

Any party is obliged to provide the necessary support and cooperation to the enterprise in

**፳፮ <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛው አካል በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ለኢንተርፕራይዙ አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**፳፯ <u>ኢንተርፕራይዙ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ኢንተርፕራይዙ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፳፰ <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብና መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፱ <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

ቦርዱ ይህንን ደንብ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የተለያዩ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፴ <u>ደንብ ስለማሻሻል</u>**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን ደንብ ማሻሻል ይችላል፡፡

**፴፩ <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከፀደቀበት ከዛሬ ጥር ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ወላይታ ሶዶ**

**ጥር ፲፩/፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

matters covered by this regulation.

**27. <u>Duration of the Enterprise</u>**

Duration of the Enterprise shall be unlimited.

**28. <u>Repealed Laws</u>**

Any rules, regulations or practices that conflict with this rule shall not apply to the matters covered by this rule.

**29. <u>Powers to Issue Directives</u>**

The Board may issue various regulations to carry out this regulation.

**30. <u>Amendment of the Regulation</u>**

The State Government Administrative Council may amend this regulation when deemed necessary.

**31. <u>Effective Date</u>**

This regulation shall come to force effective as of today, January 20, 2024, the date it was approved.

**Wolaita Sodo**

**This 20th Day of January, 2024**

**Tilahun Kebede**

**Chief Executive of the South Ethiopia Regional State**

| | |
|---|---|
| የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር | |